# የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት
የቅጥር አገልግሎቶች መምሪያ

MURIEL BOWSER
ከንቲባ

ዶ/ር UNIQUE MORRIS-HUGHES
ዳይሬክተር

## Paid Family Leave ታክስ ክፍያ መመሪያዎች

**<u>በግል የሚሰሩ ግለሰቦች(Self-Employed Individuals, SEI)</u>**

የ Paid Family Leave ቢሮ (OPFL) የግል ስራ የሚሰሩ ግለሰቦች ለ Paid Family Leave (PFL) ታክስ የክፍያውን ሂደት እንዲፈጽሙ ለመርዳት የሚከተሉት መመሪያዎች አዘጋጅቷል። በዲስትሪክቱ የPFL ፕሮግራም ውስጥ አማራጭ ያለው SEI ከሆኑ፣ የሩብ PFL ፕሮግራምም ክፍያዎን ለመፈጸም OPFL መለያ እንዲፈጥሩ እና የሰራተኛ የግል-አገልግሎት ፖርታል (ESSP) እንዲጠቀሙ ያበረታታል።

OPFL የግል ስራ ከሚሰሩ ግለሰቦች የሚከተሉትን የታክስ ክፍያዎችን ይቀበላል፦

### 1) ACH ዴቢት (ኤሌክትሮኒክ ቼክ)

በ ACH ዴቢት በኩል ለመክፈል፣ ESSP ላይ በአሰሪዎ መለያ ይግቡ፦

1. ወደ "ክፍያዎች" ትር ይሂዱ።
2. "የPFL ክፍያዎችን ይፈጽሙ" የሚለውን ይምረጡ።
3. ወደ "PFL የክፍያ መንገድ" የምርጫ ገጽ ለመሄድ የPFL ክፍያ መለያ ማጠቃለያ ገጽ ላይ "ቀጥል" የሚለውን ይጫኑ።
4. ከክፍያ ዘዴ አማራጮች ላይ "ACH ዴቢት" የሚለውን ይምረጡ።
5. ወደ አሰሪ PFL የክፍያ ዝርዝሮች ገጽ ለመቀጠል "ቀጥል" የሚለውን ይጫኑ።
6. ክፍያ ለመፈጸም ካሰቡበት አካውንት ጋር የተያያዘውን የባንክ ማዘዣ ቁጥርዎን እና የአካውንት ቁጥርዎን ያስገቡ።
   - የባንክ ማዘዣ እና መለያ ቁጥሮችን እንደገና ያስገቡ።አይገልብጡ/አይለጥፉ።
   - ክፍያ ሊከፍሉበት የሚፈልጉትን የመለያ አይነት ይምረጡ፦ "የተንቀሳቃሽ" ወይም "የቁጠባ"።
   - ክፍያ የሚደረግበትን ቀን ከመለያው አይነት አጠገብ ባለው የጽሁፍ ሳጥን ውስጥ ያስገቡ። ክፍያ የሚደረግበት ቀን OPFL የባንክ አካውንትዎን የሚሰጥበት ቀን ነው።
7. የክፍያ ውይይት መስኮቱን ለመዝጋት እና ክፍያውን ለማጠናቀቅ "ይጨርሱ" የሚለውን ይጫኑ።

| ACH ዴቢት እገዳ መረጃ |
|---|
| አንዳንድ የገንዘብ ተቋማት የደንበኛን የባንክ አካውንቶች ፈቃድ ከሌላቸው የኤሌክትሮኒክ ክፍያዎች ለመከላከል የ "ACH የዴቢት እገዳ" እንደሚጠቀሙ እባክዎ ያስተውሉ። የዴቢት ክፍያዎችን ለOPFL ከባንክ አካውንት ዴቢት እገዳ ፈቃድ ለመስጠት ካስፈለገዎት የታክስ ክፍያዎችን ለመፍቀድ፣ ከባንክዎ ጋር መነጋገር አለብዎት። የዴቢት ክፍያዎችን ፈቃድ ለመስጠት ከፈለጉ፣ እባክዎ ለባንክዎ ከዚህ በታች በተጠቃለለው የACH ዴቢት እገዳ መረጃ ያቅርቡ።<br><br>የሚከፈሉበት የቤተሰብ የፈቃድ ቢሮ፦ **Wells Fargo**<br>ACH የኩባንያ መታወቂያ፦ **D536001131**<br>ACH ኩባንያ ስም፦ **OPFL** |

## 2) በፖስታ

### በ PFL30S ቅጽ በኩል ክፍያ

PFL30S ቅጽ የኦንላይን የክፍያ ፖርታልዎን በመጠቀም የሩብ አጋማሽ PFL ታክስን ለመሰብሰብ እና ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል።

1. የ PFL30 ቅጽን https://does.dc.gov/page/dc-paid-family-leave" መርጃዎች" ላይ ያግኙ እንዲሁም የ PFL30S ቅጽን ለመሰብሰብ ከዚህ በታች ባለው አድራሻ ቢሯችንን መጎብኘት ይችላሉ።
2. የሩብ አጋማሽ ታክስዎን በ PFL30S ቅጽ ላይ የሚገኘውን መመሪያዎች በመጠቀም ያስሉ።
3. መስመር 7 ላይ የሚገኘውን "አጠቃላይ የሚላከው መጠን" ላይ የተሰላውን መጠን ቼክ ወይም የገንዘብ ማዘዣ ይጻፉ።

**PFL30S** ወደ DOES ዋና መስሪያ ቤት ፖስታ ተልኳል፦

Office of Paid Family Leave Tax Division, 3rd Floor
4058 Minnesota Avenue, NE
Washington, DC 20019

ፖስታ **PFL ታክስ ክፍያ** ለቁልፍ ሳጥን አድራሻ:

DC Government Paid Family Leave
P.O. Box 718269
Philadelphia, PA 19171

የቼክ እና የገንዘብ ማዘዣ ክፍያዎች በ**"DC Treasurer" በኩል መከፈል አለባቸው።**

### በቫውቸር በኩል ክፍያ

በቼል ወይም በገንዘብ ማዘዣ በኩል ለመክፈል፣ በESSP በአሰሪዎ መለያ ይግቡ።

1. ወደ "ክፍያዎች" ይሂዱ።
2. "የPFL ክፍያዎችን ይፈጽሙ" የሚለውን ይምረጡ።
3. ወደ "PFL የክፍያ መንገድ" የምርጫ ገጽ ለመሄድ በPFL የክፍያ መለያ ማጠቃለያ ገጽ ላይ "ቀጥል" የሚለውን ይጫኑ።
4. "የመመሪያ ወረቀት ቼክ" የሚለውን ከክፍያ መንገድ ምናሌው ላይ ይምረጡ።
5. ወደ ቼክ ወረቀት PFL ክፍያ ገጽ ለመቀጠል "ቀጥል" የሚለውን ይጫኑ።
6. የክፍያ ቫውቸርን ለመሰብሰብ እና ለማተም "ቫውቸር ያትሙ" የሚለውን ያመላክቱ እና ይምረጡ።
   - አንዴ ከታተመ፣ "የታተመ PFL ክፍያ ቫውቸር" አማራጭ አዝራርን ይጫኑ።
   - "ስኬታማ የPFL ክፍያ" የማረጋገጫ ገጽ ለመሄድ "ቀጥል" የሚለውን ይጫኑ።
7. የክፍያ ውይይት መስኮትን ለመዝጋት እና ክፍያውን ለማጠናቀቅ "ይጨርሱ" የሚለውን ይጫኑ።

**እባክዎን ልብ ይበሉ፦** እያንዳንዱ የቼክ ክፍያ በ ESSP ከሚደረግ ክፍያ ቫውቸር የታገዘ መሆን አለበት። የክፍያ ቫውቸር "**የፖስታ ምልክት ቀን**" መስክ፣ ቼኩ በፖስታ የተላከበትን ቀን ማመላከት አለበት። የገባው የፖስታ ምልክት ቀን እቃው በፖስታ ከተላከበት ቀን ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት። የፖስታ ቀን ምልክት አለመኖር የክፍያዎን ሂደት ያዘገያል እና ቅጣቶችን እና/ወይም በሂሳብዎ ላይ ወለድን ሊያስከትል ይችላል።

ሁሉም ቼክ እና ገንዘብ ማዘዣ ክፍያዎች ለ **"DC Treasurer"** መከፈል አለባቸው እናም ከላይ ወደተገለጸው የቁልፍ ሳጥን አድራሻ መላክ አለባቸው። ***ማስታወሻ: ተቀባይነት የሌላቸው/የተመለሱ የACH ዴቢት እና ተገቢ ያልሆኑ ቼኮች ጋር የተያያዘ የ$65 ተጨማሪ ክፍያ አለ።***